# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ታህሳስ 4/2006

## የሕዝብን ዋና ጠላት ስም ለማደስ መጣር ወንጀል ነው!

ሕዝብን የፈጀ ፋሺስት፤ የአረመኔ አረመኔ፤ ጨካኝ ነፍሰገዳይ፤ ፈሪ ፈርጣጭ መንግስቱ ኃይለማርያምን ነፍስ ሊዘሩበትና የቆሸሸ ታሪኩን ለማደስ ብቅ ብቅ ብለው የነበሩትን ሁሉ ስንታገላቸው ቆይተናል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የእነ ሂትለርና የነሙሶሊኒን ታሪክ ለማደስ ከሚደረገው ጸያፍ ጥረት የተለየ አይደለም። ይህን ነፍሰ ገዳይ ሰው ነው ብለው መጽሐፉን ያተሙለትና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በቃለ መጠይቅ ሽፋን መድረክ ሊሰጡት የተነሱትን ሁሉ ኢሕአፓ ከመቃወም ሌላ ጥረታቸውን ለማክሸፍ እንደሚታገላቸው ከወዲሁ ይነግራቸዋል።

ፋሺስቱ ኮሎኔል አረመኔ ነፍሰ ገዳይ የሆነውን ያህል ዓይኑን በጨው ሳያጥብ የሚዋሽ ማፈሪያ ግለሰብ ሆኖ የተጋለጠ ነው። ማንዴላን እንዲህ አልኩት እሱም እንዲህ ጠየቀኝ፤ የሀብታም ሀገር መሪ ለመሆን የደረሰውን መቶ ሺ ዶላር ሰጠሁት (ራሱ ሲፈረጥጥ ግን በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ዘርፎን ሄዷል !)፤ በእስር ስለነበረና ዜና ስለማያገኝ (!!) ስለ ሶሻሊስት ጎራ ዜና ጠየቀኝ ወዘተ… ብሎ የለፈፈው ሁሉ ሀሰትና  የፈጠራ ታሪክ መሆኑ ግልጽ ነው። ለነገሩ ደገፍኳቸው ያላቸው የደቡብ አፍሪካ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ፋሺስቱን የማይወዱ መሆናቸውን የደበቁ ሳይሆን ሙጋቤ ራሱ ጥገኝነት የሰጠው በአሜሪካ (በሄርማን ኮህን) ጥያቄ መሰረት መሆኑን በዚምባብዌ ያለው የአሜሪካ አምባሳደር ሰሞኑን ገልጿል። በሕዝባችን ደም ሊቀልዱ የተነሱ የዚህን አረመኔ መጽሐፍ ቢያትሙለትም የተባለው መጽሐፍ በውሸት ትረካ የተሞላ  በመሆኑ የሚያነበው አጥቶ ዳግም ውግዘትና ውርደትን ተከናንቧል። ይህን አረመኔ የሚያደንቁና አገዛዙንም የሚመኙ ማወቅ ያለባቸው አቢይ ሀቅ ሰማይ ከመሬት ቢጋጠም የፋሺስቱ ደርግ ስርዓት መቸም ቢሆን መቼ በሕዝባችንና በሀገራችን ላይ ዳግም የማይጫን መሆኑንና ይህ ስርዓት ተመልሶ እንዳይመጣ ሕዝብና ኢሕአፓ በሙሉ ትኩረት የሚታገለው መሆኑን ነው። ምኞት ከንቱ እንላቸዋለን።

ፋሺስቱን  ኮለኔል የሚያዳንቁ በተጨፈጨፈው ሕዝባችን ላይ የሚያላግጡ ናቸውና ከሕዝብ ጎራ ነን የሚሉት ከቅጥፈት አልፎ ውግዘት የሚገባው ይሆናል። ድጋፍ ፍለጋ ከፋሺስቱና ከርዝራዦቹ ጋር የሚተቃቀፉ ሁሉ ሕዝብን ተጻረዋልና ሕዝብም በዝምታ የሚያልፋቸው አይሆኑም። ለሙሶሊኒ ሐውልት ሲሰራ እሪ ያለ ዜጋ ሁሉ ዛሬ የቀይ ሽብሩ ዋና አቀንቃኝና ሀገርን የካደ፤ ስንቱን ዜጋና መኮንኖችንም የጨፈጨፈ፤ ሀገርን ለሌላ ጠላት አጋልጦና ገንዘቧን ዘርፎ የፈረጠጠ ፋሺስቱን ኮሎነል መድረክ አምጥተው ታሪኩን ሊያድሱ የሚጥሩትን ሁሉ ማውገዝ ግደታው ነው። የሰማዕት ደም ለዚህ ተቃውሞና ግዳጅ ይጠራናል። ደርግም ኢሰፓም ወድመዋል በሕዝብ ትግል ። ማንም ቢለፋ ቢቀላምድ ነፍስ ሊዘራባቸው አይችልም።

ፋሺስቱ ኮሎኔል ለፍርድ ይቅረብ!

ሽብርተኞችና ነፍሰ ገዳዮች ተጋልጠው ለፍርድ ይቅረቡ!

ክብር ለሰማዕታት !!


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217    fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France